



## በሲያትል ውስጥ ቤት ስለመከራየት

## መብቶች፣ ኃላፊነቶች፣ ሀብቶች

### ተከራዮች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፡-

- ደህንነቱ በተጠበቀና በአግባቡ በተያዘ ቤት ውስጥ የመኖር
- ከአድልዎ ወይም ከብቀላ እርምጃ ነጻ የመሆን
- አከራዩ ቤቱን ለመጎብኘት ሲፈልግ ተገቢ ማሳወቂያ እንዲሰጥ የማድረግ
- በሕገ ወጥ መንገድ ከይዞታው ያለመነቀል
- በኪራይ ስምምነቱ ላይ ለውጥ ሲደረግ የጽሁፍ ማሳወቂያ የማግኘት

### የተከራዮች ኃላፊነት፡-

- ኪራይ የመክፈል
- ንብረቱን ያለመጉዳት
- የኪራይ ስምምነቱን ደንቦች የማክበር
- ለንብረቱ ባለቤትና ለስራ አስኪያጁ ምክንያታዊ የሆነ ንብረቱን የመጎብኘት ዕድል የመስጠት

ስለመብቶችዎና ኃላፊነቶችዎ ተጨማሪ መረጃ ከዚህ ያግኙ፡-

**www.seattle.gov/rentinginseattle**

## ያነጋግሩን

**ድረ ገጽ**
www.seattle.gov/RRIO

**ስልክ ቁጥር**
(206) 684-4110

**ቲቲዋይ**
7-1-1 ወይም (206) 233-7156

**በፖስታ ወይም በአካል**
700 Fifth Avenue, 20th Floor
PO Box 34234
Seattle, WA 98124-1234

## የተተረጎሙ ቅጂዎችን ማግኘት ይቻላል

Amharic (አማርኛ) • Cambodian/Khmer (ភាសាខ្មែរ) Chinese (中文 ) • Korean (한국어) • Lao/Laotian/ Phaasaa Laao (ພາສາລາວ) • Oromiffa • Russian (русский язык) • Somali/af Soomaali • Spanish (Español) • Tagalog • Thai (ภาษาไทย) • Tigrinya (ትግርኛ) Vietnamese (Tiếng Việt)

City of Seattle
Department of Construction & Inpsections

# የኪራይ ቁጥጥር መረጃ



# የኪራይ ምዝገባና ቁጥጥር ስርዓት (RRIO)

*ለሁሉም የሲያትል ተከራዮች ደህንነቱና ጤናማነቱ የተጠበቀ ቤትን ማሻሻልና ማቅረብ*

## ቤቴ ቁጥጥር የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

የኪራይ ቤት ዝግጁነትና ጥራት ማረጋገጥ ሲያትልን ምርጥ የመኖሪያ ቦታ ያደርጋታል። የኪራይ ምዝገባና ቁጥጥር ስርዓት (RRIO) ፕሮግራም በሲያትል ውስጥ ያለው የኪራይ ቤት ሁኔታ ደህንነቱ የተጠበቀና መሰረታዊ የአያያዝ መስፈርቶችን ማሟላቱን ለማረጋገጥ ያግዛል። ፕሮግራሙ የተቀረጸው ተከራዮች አያያዛቸው ከደረጃ በታች በሆኑ ቤቶች ውስጥ እንዳይኖሩ ለመከላከል ነው።

**ቤትዎ አስተማማኝ በሆነ መንገድ መያዙን ለማረጋገጥ፣ ቁጥጥር ሊያስፈልግ ይችላል። የፍተሻ ሥራውን የማከናወን ኃላፊነት የንብረቱ ባለቤት ወይም የሥራ አስኪያጁ ነው።**



## የፍተሻ ሥራውን የሚያከናውነው ማነው?

የፍተሻውን ተግባር የሚያከናውነው፡-

- የከተማ ኢንስፔክተር
- ሥራው በከተማው ቁጥጥር የሚደረግበት ስልጡን የግል ኢንስፔክተር

## ቁጥጥር ምንድን ነው?

በኪራይ ምዝገባና ቁጥጥር ስርዓት (RRIO) የሚከናወን ፍተሻ መሰረታዊ የቤት አያያዝ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ የመፈተሽ ሒደት ነው። ኢንስፔክተሩ ከሚፈትሻቸው ጉዳዮች መካከል፡-

- በጣሪያው ወይም ግድግዳው ላይ ቀዳዳ ወይም የሚታይ የፍሳሽ ስርቀት አለመኖሩን
- እንደ ሲንክ እና መጸዳጃ ቤት የመሳሰሉ የቧንቧ መስመሮች መስራታቸውን
- መስኮቶችና በሮች በትክክል መስራታቸውንና አስተማማኝነታቸውን
- በቋሚነት የተገጠመና የሚሰራ የማሞቂያ ሲስተም መኖሩን

ፍተሻ ማለት ንብረትዎን መፈተሽ፣ አኗኗርዎን ማጥናት ወይም መኖሪያ ቦታዎ ውስጥ ምን እንደሚሰሩ ማየት አይደለም።

ሙሉ የፍተሻ ቼክሊስቱን በቀጣዩ ድረ ገጽ ላይ ያገኛሉ **www.seattle.gov/RRIO**።

### የኪራይ ምዝገባና ቁጥጥር ስርዓት (RRIO) ኢንስፔክተር የሚከተሉትን ያከናውናል፡-

- በቤቱ ውስጥ ያሉ ክፍሎችን በሙሉ መመልከት
- ውጫዊ አካባቢዎችን መመልከት
- ከሲንኮቹ ስር ወይም ከፈርኒቸሩ በስተጀርባ ሊመለከት ይችላል

### የኪራይ ምዝገባና ቁጥጥር ስርዓት (RRIO) ኢንስፔክተር የሚከተሉትን ነገሮች አይፈጽምም፡-

- የግል ንብረትዎን መበርበር
- መሳቢያዎች ወይም ሌሎች ዕቃዎችን መፈተሽ
- ስለ ኢምግሬሽን ሁኔታዎ ወይም ሕገ ወጥ ተግባራት እርስዎን መጠየቅ

## የፍተሻ ሥራው የሚከናወነው እንዴት ነው?

### 1 ማስታወቂያ

ከንብረቱ ባለቤት ወይም ከሥራ አስኪያጁ ቢያንስ የሁለት ቀናት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሊደርስዎ ይገባል።

ወደሚፈተሸ ቤት ውስጥ እንዴት መግባት እንደሚቻል ከንብረቱ ባለቤት ወይም ከሥራ አስኪያጁ ጋር ዕቅድ መንደፍ አለብዎ። በከተማዋና በግዛቱ ሕጎች መሰረት፣ ያለበቂ ምክንያት ኢንስፔክተር ወደቤት እንዳይገባ መከልከል የለብዎትም።

### 2 ማዘጋጀት

መጠገን ስላለበት ማንኛውም ነገር በቅድሚያ የንብረቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ እንዲያውቅ ያድርጉ።

ኢንስፔክተሩ የቤቱን ክፍሎች በሙሉ ለማየት መቻሉን ያረጋግጡ። እንዲታይብዎ የማይፈልጉትን ማንኛውም የግል ንብረት ያርቁ።

### 3 መግባት

የፍተሻ ሥራው በሚከናወንበት ወቅት ኢንስፔክተሩ ወደቤትዎ መግባቱን ያረጋግጡ።

በፍተሻው ወቅት በቦታው ለመገኘት ወይም ላለመገኘት የመወሰን መብት አለዎ።

### 4 ክትትል

የንብረቱ ባለቤት እና ሥራ አስኪያጁ የፍተሻውን ውጤት እንዲያውቁት ይደረጋሉ። ንብረቱ ፍተሻውን ማለፉን ለማረጋገጥ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ **www.seattle.gov/sdci** ። "find Status and Activity" (ኣድራሻኹም የእትዉ) በሚለው መፈለጊያ ውስጥ ያስገቡ።

በፍተሻው ወቅት ያጋጠም ችግር ካለ፣ ወይም ሳይታይ የታለፈ የጥገና ወይም የደህንነት ጉዳይ ካለ፣ ለንብረቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ማሳወቅ ወም ለኪራይ ምዝገባና ቁጥጥር ስርዓት (RRIO) ፕሮግራም በስልክ ቁጥር **(206) 684-4110** ደውለው ማሳወቅ ይችላሉ።

